# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት

አቅራቢዎች



## ከአሳዳጅነት እስከ ስብከት

ጸሐፊው: Edward Hughes

ምሣሌ አቅራቢው: Janie Forest, Alastair Paterson

ያሻሻለው (አሻሻሎ የጻፈው): Ruth Klassen

የተተረጎመው: Zemendale Translation Service
email: zemendale@gmail.com
Po Box 32155, Addis Ababa, Ethiopia

አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org

©2022 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።



በጥንቷ ቤተክርስቲያን
እግዚአብሔር ታላለቅ ነገሮችን
በጸሎት ውስጥ አድርጓል።

ፊሊጶስ የሚባል አንድ ሰው
እጅግ በተጨናነቀ ከተማ
ውስጥ ሆኖ ፣ ስለ ኢየሱስ
ይናገር ነበረ። ነገር ግን
እግዚአብሔር ወደ በረሃ
አወጣው። ለምን?



በበረሃ መሐከል እየተጓዘ ያለ አንድ
ተጓዥ እንዳለ እግዚአብሔር አውቋል ፤
እርሱም በኢትዮጲያ ያለች ንግስት
ታዛዥ የሆነ ሰው ነበረ፡፡ እርሱም
በመንገዱ እያለ ፣ እጅግ ልዩ የሆነን
መጽሐፍ ያነብብ ነበረ፡፡ መጽሐፉ ምን
ሊሆን እንደሚችል ልትገምት ትችላለህ?



ፊሊጶስ
እግዚአብሔርን
ሲታዘዝ ፤
የእግዚአብሔርን
ቃል እያነበበ ግን መረዳት
ያቃተውን ሰው እንዲያግዘው ብሎ
ወደዚያ ሰው ላከው፡፡ እርሱም
ፊሊጳስ እንዲያግዘው ጋበዘው፡፡

ገዢውም እንደህ ሲል ፊሊጶስን ጠየቀው ፣ “ይሔ ምን ማለት ነው;” ሰረገላውም በበረሃው መንገድ እያለ ሲንገጫገጭ ፣ ፊሊጶስ አፉን ከፈተ እና ያንን መጽሐፍ ከፍቶ ስለ ኢየሱስ ያስተምረው ጀመረ፡፡





አፍሪካዊውም ገዢ ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምኖ የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል አመነ። አንድ ውኃም አይቶ ፣ እንዲህ አለው ፣ “በዚህ እንዳልጠመቅ ማን ያግደኛል?”

ከዚያም ፊሊጶስ ፣ “በሙሉ ልብሕ የምታምን ከሆነ ፣ ትችላለህ፡፡” ገዢርውም፣ “ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ፡፡” ብሎ መለሰ፡፡ ፊሊጶስም ወደ ውኃ ወሰደውና አጠመቀው፡፡





ከውኃው ውስጥ ከወጡ በኋላም ፣ የጌታ
መንፈስ ፊሊጶስን ነጠቀው ፤ አፍሪካዊው
ገዢም ከዚያ በኋላ አላየውም፡፡ እርሱም
ወደ ኢትዮጲያ በደስታ ተመለሰ፡፡

ነገር ግን አንዳንድ ሰዎች ክርስቲያኖችን ይጠሏቸው ነበረ ፤ የፊሊጶስ ወዳጅ የሆነ ፣እስጢፋኖስ ስለ ኢየሱስ ሲያወራ ደስ በማይላቸው የተበሳጩ ሰዎች ተገድሏል፡፡ ከጠርሴስ የሆነ ሳውል የሚባል ሰው እስጢፋኖስ ሲገደል ተባብሯል፡፡ ሳውል ክርስቲያኖችን ሁሉ ይጠላ ነበረ፡፡



ሳውል ፣ ዛቻንና ግድያን በክርስቲያኖች ላይ እያደረገ ፣ ኢየሱስን የሚከተሉ ወንዶችንና ሴቶችን ለማሰር ፣ ከሊቀ ካሕናቱ የይሁንታን ደብዳቤ ለመቀበል ወደ ሊቀካህናቱ ሔደ፡፡





ምስኪኑ የጠርሴሱ ሳውል !
የእግዚአብሔርን ሕዝብ
ሊጎዳ ሲፈልግ ፣ ኢየሱስ
ራሱን እያሳደደ እንደሆነ
አላወቀም ነበረ።
እግዚአብሔር ሳውልን
ማስቆም ነበረበት። ነገር
ግን እንዴት?

እግዚአብሔር ሳውልን
“ያዘው” ! ሳውል በደማስቆ
በምትባል ከተማ መንገድ ላይ
እያለ ፣ እግዚአብሔር ከሰማይ
ብርሐንን አሳየው። ሳውልም
በምድር ላይ ወደቀ ፤ ከዚያም
ድምጽን ሰማ።





ሳውልም እየጮኸ፣ “ጌታ ሆይ አንተ ማነህ;” አለ፡፡ “እኔ አንተ የምታሳድደኝ ኢየሱስ ነኝ አለው፡፡” እየፈራና እየተደነቀ ፣ ሶውል እንዲህ ብሎ ጠየቀ ፣ “ጌታ ሆይ ፣ ምን እንዳደርግልህ ትፈልጋለህ;” ጌታም እንዲህ አለው ፤ “ተነስና ወደ ከተማ ግባ ፤ ምን ማድረግ እንዳለብህም ይነግሩሃል፡፡”

ከሳውል ጋ የነበሩ ሰዎች ሁሉም ድምጹን ሰምተዋል ፤ ነገር ግን ማንንም አላዩም ነበረ። ሳውልም ከመሬት ላይ ሲነሳ አይኑ እንደታወረ አወቀ! ወደ ደማስቆም መንገድ መሩት።



በከተማው ውስጥ ፣ አይነ ስውር
ሆኖ ሳይበላ ሳይጠጣ ሶስት
ቀናትን ቆየ፡፡ ምንአልባት
በደማስቆ መንገድ ወደ ተገናኘው
ኢየሱስ ኢየጸለየ ይሆናል፡፡



እግዚአብሔር ሁሉን ነገር አቅዷል፡፡
በደማስቆ አናኒያ የሚባል ደቀመዝሙር
ነበረ፡፡ ጌታም ሳውልን እንዲያግዘው
ልኮት ነበረ፡፡ አናኒያም አጅግ ፈርቶ
ነበረ፡፡ ነገር ግን ታዘዘ፡፡ በሳውል ላይ
እጁን ሲጭን ፤ እውርነቱ ተነሳ ፤
ሳውልም በእግዚአብሔር
ቅዱስ መንፈስ ተሞላ፡፡



ሳውልም ተጠመቀ ፤ በላም። ምግብም ሲበላ ፣ በረታ። ሳውል ጥንካሬ አስፈልጎት ነበረ። እጅግ ጠቃሚ የሆነ ማድረግ ያለበት ነገር ነበረ።



በፍጥረነትም ሳውል በምኩራብ ውስጥ ሆኖ
ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን
ይሰብክ ነበረ። ይሰሙት የነበሩ ሁሉ
ይደነቁ ነበረ ፤ እንዲህ አሉ ፣ “ክርስቲያኖችን
ያጠፋ የነበረው ይሔ አይደለምን;”
አንዳንዶቹም ሊገድሉት አሴሩ።





የሳውል አዲሶቹ ጠላቶቹ ምንአልባት አምልጦ ከተማይቱን ጥሎ ይወጣ እንደሆነ ብለው ፣ ቅጥሩን ይጠብቁ ነበረ፡፡ ነገር ግን አዲሶቹ ወዳጆቹ የሆኑት ክርስቲያኖች ፣ በትልቅ ቅርጫት አድርገው በምሽት ከከተማው ቅጥር ውጪ አወጡት፡፡ ከዚያም በኋላ ፣ የክርስቲያኖች አሳዳጅ ሳውል የአዲሱ አዛዥ ፣ የጌታ ኢየሱስ ታማኝ ተከታይ ሆነ፡፡

ከአሳዳጅነት እስከ ስብከት

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ሐዋ 8-9

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

መጨረሻ

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን ግሩም ስለሆነው አምላካችን እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው፡፡

እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር እንዳደረግን ያውቀዋል፡፡ የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን አንዱንና ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት እንዲከፍል አደረገው፡፡ ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ! ያላመንን እኛም በኢየሱስ አዳኝት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል ብለምነው ይቅር ይለናል፡፡ ደግሞም ያደርገዋል፡፡ እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤ እኛም በእርሱ ውስጥ ለዘላለም እንኖራለን አሜን፡፡

ይህ እውነት እንደሆነ ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት ለመሞት ስትል ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ፡፡ እባክህ ወደ ህይወቴ ግባ ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን ይኖረኛል አንድ ቀን ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር ወደ አንተ እመጣለሁ፡፡ ለአንተ እንድኖርና እንደ ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ፡፡ አሜን፡፡

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16